# ራስ ምታት…

አልጋ ላይ ተኝቼ፣ አግድም ተንገሮርግጌ
ራሴን ሲያመኝ ውሎ፣ ዋግምት ፈልጌ
'ና እስቲ ልየው' ብለሽ፣ መነጽር አጥልቀሽ
ጸጉሬን ደባብሰሽ፣ ቦታውን ፈልገሽ፣
ወይም አልበጣሽው፣ ወይ አልሰነጠቅሽው፣
ምነዋ እህቴ ደባብሰሽ የተውሽው?
ተይኝ! ተይኝ! እህቴ
ባሰ ራስ ምታቴ…



ከአልጋው አስተኝተሽ፣ ጭንሽን አንተርሰሽ
የታመመው ራሴን በእጅሽ ደባብሰሽ
ቦታውን አግኝተሽ፣ በጣትሽም ጠቁመሽ፣
ወይን አልቆረጥሽው፣ ወይ አልቧጨርሽው
ምነዋ እህቴ፣ ቆነጣጥጠሽ ተውሽው?
ተይው! ተይው! እህቴ
ባሰ ራስ ምታቴ…



ድሮ የማላውቀው ራስ ምታት ታምሜ፣
ከጭንሽ ተኝቼ፣ አንገቴን ቆልምሜ
ምንም አልተሻለኝ፣ ምኑን አገግሜ
ወይን አልነከስሽው፣ ወይ አልተነኮስሽው
ምነዋ እህቴ፣ ነካክተሽ የተውሽው?
ተይኝ! ተይኝ! እህቴ
ባሰ ራስ ምታቴ…

ገ/ኢ. ጐርፉ።